# የ King County
# የክትባት ማረጋገጫ
# ደንብ የመሣሪያ ስብስብ

## (አማርኛ ስሪት)

በ Seattle Metropolitan Chamber of Commerce (Seattle ሜትሮፖሊታን የንግድ ምክር ቤት የተዘ) ጋጀ ይዘት

Public Health
Seattle & King County


1. ህጎቹን ይወቁ
2. ተቀባይነት ያላቸው የክትባት እና የምርመራ ማስረጃዎች
3. የትግበራ ዕቅድ ይፍጠሩ
4. ከሠራተኞች እና ከደንበኞች ጋር መነጋገር
5. ምስለ ሁኔታዎች
6. ምልክት
7. መገልገያዎችን ያግኙ
8. በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎች



# ህጎቹን ይወቁ

*ይፋዊ የ King County Health Order (የ King County የጤና ደንብ) ን [እዚህ ጋር] በመጫን ያንብቡ። ደንቡ በእንግሊዝኛ ብቻ ነው። ማጠቃለያ ከታች ቀርቧል።*

## መቼ ይጀምራል፡-

ኦክቶበር 25፣ 2021። ከ 12 የሚያንሱ የመቀመጫ አቅም ያላቸው የቤት ውስጥ ምግብ ቤቶች፣ ቡና ቤቶችና ማደሪያ ቤቶች ዲሴምበር 6፣ 2021 ስራ ይጀምራሉ።

## ተግባራዊ የሚሆነው ለማን ነው፡-

ዕድሜያቸው 12 እና ከዚያ በላይ የሆኑ ግለሰቦች። መድልዎ በቸልታ አይታለፍም። የንግድ ድርጅቶች በዘር፣ በብሔር አመጣጥ፣ በሃይማኖት፣ በጾታዊ ዝንባሌ፣ በፆታ፣ በአካለ ስንኩልነት ወይም በእድሜ ላይ በመመስረት የክትባት ማስረጃዎችን ይበልጥ በጥንቃቄ መመርመር አይችሉም።

## መቼ ያልቃል፡-

አጠቃላይ ደንቡ ቋሚ ይሆናል ተብሎ አይጠበቅም። ከስድስት ወር በማይበልጥ ጊዜ ውስጥ፣
ከኦክቶበር 25-2021 ጀምሮ፣ ይህ ፖሊሲ ወደፊት በሚከሰት የወረርሽኝ ሁኔታ ላይ ተመሥርቶ ሊራዘም ይችል ይሆናል።

## የት ተግባራዊ ይሆናል፡-

- የቤት ውስጥ ምግብ ቤቶችና መጠጥ ቤቶች እንዲሁም የወይን ጠጅ፣ ቢራና መጠጥ መቅመሻ ክፍሎች
- በሥነ ጥበብ እና በመዝናኛ ቦታዎች
- እንደ ዮጋ፣ ዳንስ፣ እና የማርሻል አርት የመሳሰሉ የአካል ብቃት እንቅስቃሴ ስቱዲዮዎችን ጨምሮ ስፖርት ቤቶች፣ ከ 500
- ሰው በላይ የሚሳተፍባቸው የውጪ ዝግጅቶች የስፖርት ውድድሮችን፣ የሙዚቃ ዝግጅቶችንና ትርዒቶችን ጨምሮ
- ለግል ጉባዔዎች የሚከራዩ የቤት ውስጥ የዝግጅት ቦታዎች ለምሳሌ ሰርጎች እና ድግሶች በእነዚህ ንግዶች ላይ የሚዘጋጁ በዚህ ደንብ ውስጥ የሚካተቱ እንደ ምግብ ቤት፣ የሙዚቃ ቦታ ወይም የመዝናኛ ተቋም
- የቦውሊንግ ቦታዎች

Public Health
Seattle & King County

# የክትባት ማስረጃ ወይም ኔጌቲቭ የምርመራ ውጤት የሚያስፈልገው የት ነው?

| ቦታ (ይህ የተሟላ ዝርዝር አይደለም) | ያስፈልጋል | በጥብቅ ቢመከርም አስፈላጊ አይደለም | አያስፈልግም |
|---|---|---|---|
| የቤት ውስጥ መመገቢያ ያላቸው መጠጥ ቤቶችና ምግብ ቤቶች | X | | |
| የፊልም ቲያትር ቤቶች፣ ጂምናዚየሞች እና የቤት ውስጥ የአካል ብቃት እንቅስቃሴ ቦታዎች፣ የቤት ውስጥ የስነ-ጥበብ የትርዒት ማሳያ ቦታዎች፣ የቤት ውስጥ ትልልቅ ስብሰባዎች ወይም ኮንፈረንሶች | X | | |
| የቤት ውስጥ የመዝናኛ ቦታዎች (ለምሳሌ፡- የቦውሊንግ መጫወቻዎች፣ የመዝናኛ ጨዋታ ማዕከላት፣ የቤት ውስጥ የእግር ኳስ መድረኮች፣ ወዘተ) | X | | |
| ከ 500 በላይ ሰዎች የሚሳተፉበት የውጪ ስፖርት ወይም መዝናኛ ዝግጅቶች | X | | |
| በንግድ ቦታ የሚደረጉ የግል ዝግጅቶች፣ ሠርግና ግብዣዎች (ለምሳሌ የሠርግ ቦታ፣ ምግብ ቤት ወይም የሙዚቃ ቦታ) | X | | |
| በግል ቤት ወይም በእምነት ድርጅት የሚደረጉ የግል ዝግጅቶች ፤ ሰርግና ግብዣዎች | | | X |
| ከቤት ውጭ መመገቢያ ስፍራ፣ ምግብ ከውጪ መውሰድ፣ የምግብ ሜዳዎች | | | X |
| ሰራተኛ ወይም የትምህርት ቤት ካፊቴሪያዎች፣ የመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የስፖርት ውድድሮች | | | X |
| የእምነት ድርጅቶች | | X | |
| የሸቀጥ ሱቆች | | X | |
| ከቤት ውጭ የመንገድ ትርዒት፣ የምሽት ገበያ፣ ወይም ገበሬዎች ገበያ | | | X |

## ያልተካተቱ

- ለአንደኛ ደረጃ፣ ለመካከለኛ ደረጃ እና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በውጭ ወይም በቤት ውስጥ የሚደረጉ የወጣቶች ስፖርታዊ ውድድሮች እንዲሁም በእነዚህ ዝግጅቶች ላይ ተመልካቾች
- ከቤት ውጭ መመገብ
- ከምግብ ቤቶች የሚሄዱ ምግቦች፣ መጠጥ ቤቶች እና ቡና ቤቶች ውስጥ ካፌዎች፣ ዴሊስ፣ የቡና ሱቆች ይገኙበታል
- እንደ አውሮፕላን ማረፊያ፣ የገበያ ማዕከል የምግብ ሜዳዎችና የትምህርት ቤት ካፊቴሪያዎች ላሉ በህንፃ ውስጥ የሚገኙ የቤት ውስጥ መመገብያዎች በዋናነት ግን ለመመገብያነት የማይውሉ
- የቀብር ሥነ-ስርዓቶች
- ሰርጎች፣ ከላይ ከተጠቀሱት የህዝብ የቤት ውስጥ ተቋማት ውስጥ ከሚፈፀሙት ውጪ። ይሁን እንጂ፣ የክትባት ማስረጃ ወይም የ Covid-19 ምርመራ ኔጌቲቭ ውጤት ሰነድ አጥብቆ ይመከራል።
- ከላይ ከተጠቀሰው ማናቸውም የህዝብ የቤት ውስጥ ተቋማት ውስጥ ከሚከሰቱ በስተቀር በእምነት ላይ የተመሰረቱ ስብሰባዎች። ይሁን እንጂ፣ የክትባት ማስረጃ ወይም የ Covid-19 ምርመራ ኔጌቲቭ ውጤት ሰነድ አጥብቆ ይመከራል።
- በ King County ምርጫዎች የፀደቁ የድምፅ ማዕከላት፣ በማንኛውም ቦታ ይካሄዳሉ።

## ሙሉ በሙሉ መከተብ

*"ሙሉ በሙሉ መከተብ" ማለት፡-*

- *አንድ ሰው የሚያስፈልገውን የክትባት መጠን በሙሉ ተቀብሏል ማለት ነው ይህም በ Food and Drug Adminstration (FDA፣ የምግብ እና የመድሀኒት አስተዳደር) የፀደቀ የ Covid-19 ክትባት (የModerna ወይም Pfizer-BioNTech ክትባቶች ሁለት የክትባት ዶዝ ወይንም የ Johnson & Johnson ክትባት አንድ ዶዝ)*
- *በ World Health Organization (WHO፣ የአለም ጤና ድርጅት) ፈቃድ ያገኘ የ Covid-19 ተከታታይ ክትባት፣ እናም ከመጨረሻው የክትባት ዶዝ በኋላ 14 ቀናት አልፈዋል።"*



# ተቀባይነት ያላቸው የክትባት ማስረጃዎች

# ተቀባይነት ያላቸው የክትባት ማስረጃዎች




የክትባት ካርድ ፎቶ




የክትባት ካርድ




ከክትባት አቅራቢው ወይም MyIRmobile.co ፕሪንት የተደረገ መረጃ




በ 72 ሰአታት ውስጥ የተወሰደ ኔጌቲቭ የ COVID ምርመራ ውጤት



# ተቀባይነት ያላቸው ኔጌቲቭ የምርመራ ውጤት ማስረጃዎች

# ተቀባይነት ያላቸው ኔጌቲቭ
# የምርመራ ውጤት ማስረጃዎች

- የህትመት ወይም የዲጂታል ሰነድ ከ፡-
  - መድህኒት መደብር
  - የቤተ ሙከራ
  - ምርመራ አቅራቢ
- በ FDA ተቀባይነት ያገኘ የ PCR ምርመራ በቀደሙት 72 ሰዓታት ውስጥ ተወስዷል
- በ FDA የተቀባይነት ያገኘ ፈጣን ምርመራ በዝግጅት ቦታው ላይ የሚገኝ ምርመራ አቅራቢ




**በ 72 ሰአታት ውስጥ የተወሰደ ኔጌቲቭ የ COVID ምርመራ ውጤት**



# የትግበራ ዕቅድ ይፍጠሩ

Public Health
Seattle & King County

እያንዳንዱ ንግድ የሚሰራው በተለያየ መንገድ ቢሆንም ይህንን አዲስ ፖሊሲ ያለምንም ችግር ተግባራዊ ለማድረግ አስቀድሞ እቅድ ማውጣት አስፈላጊ ነው።

- [ ] ሠራተኞች የሚሰበሰቡበትን ቀንና ሰዓት እንዲሁም አስፈላጊውን ሥልጠና ይለዩ።
- [ ] የእርስዎ ንግድ የ King County ን ደንብ እንደሚያከብሩ ለደንበኞችዎ የሚያሳይ ምልክት ይስቀሉ።
- [ ] ሠራተኞች ለደንበኞች ማረጋገጫ ለመጠየቅ በጣም ተስማሚ ጊዜን እንዲለዩ ለይተው ከሰራተኞችዎ ጋር መነጋገር።
- [ ] የስብሰባው ቦታ ፈጣን ምርመራ የሚያደርግበት ከሆነ ፤ አንድን ሂደት በመዘርዘር ፤ እንዲሁም ይህን ሂደት ከሠራተኞችዎ ጋር ይነጋገሩበት።
- [ ] ትክክለኛ የ Covid-19 ክትባት ማረጋገጫዎችን እንደሚያውቁ ለማረጋገጥ እና ስለ ፀረ-መድልዎ ፖሊሲዎች ከሠራተኞች ጋር ስልጠናዎችን ያካሂዱ።
- [ ] ከሠራተኞች ጋር ሊሆኑ ስለሚችሉ ሁኔታዎች ይነጋገሩ (በ "ምስለ ሁኔታዎች" ክፍል ውስጥ ሀሳቦችን ይመልከቱ)።





Public Health
Seattle & King County



# ከሠራተኞች ጋር መነጋገር

# ሰራተኞችን ማሰልጠን

- የፖሊሲ ለውጥ ምክንያቶችን ለማጋራት እና ለጥያቄዎች መልስ ለመስጠት የቡድን ስብሰባ ያድርጉ።
- ለሁሉም የቡድን አባላት የመተግበር እቅድ እና በመገልገያዎች ክፍፍል ላይ የጽሁፍ መልዕክት ይላኩ።
- የ King County ን ደንብ እና የሰራተኞችን መገልገያዎች ፖስተር ከፍባለና በሚታይ ቦታ ላይ ይለጥፉ።
- ሠራተኞች ጥያቄ የሚጠይቁባቸውን መንገዶች ያቅርቡ
- King County ከደንበኛው/ከሸማቹ ጋር የሐሳብ ልውውጥ ለማድረግ በተለያዩ ቋንቋዎች ተለጣፊ ምልክቶችን እያቀረበ ነው። ሁሉም ሠራተኛ የበርካታ ቋንቋዎች መገልገያዎች የት እንደሚገኙ ማወቅ ይኖርበታል። በእያንዳንዱ ቋንቋ አንድ በማስጠረዝ እንደ ምሳሌ ውሰድ።

KC Vax Verified Webinar (የ KC Vax የተረጋገጠ የኢንተርኔት ጉባኤ)

*የኢንተርኔት ጉባኤው በእንግሊዘኛ ብቻ ነው*



# ከደንበኞች ጋር የሐሳብ ልውውጥ ማድረግ

ለሠራተኞችም ሆነ ለደንበኞች እነዚህ እርምጃዎች እየተወሰዱ ያሉት ለምን እንደሆነ ማወቅ አስፈላጊ ነው ።
ለሠራተኞችዎና ለደንበኞችዎ ሊያካፍሏቸው የሚመከሩ አንዳንድ መልእክቶች ከዚህ በታች ቀርበዋል።

## ለምን?

- የንግድ ማህበረሰብ እንደመሆናችን መጠን ፤ የንግድ ድርጅቶችን ክፍት በማድረግ እና እድገታችንን እና ስኬታችንን የሚያረጋግጡትን ሠራተኞቻችንን ፣ ደንበኞቻችንን እና የማኅበረሰቡን አባላት ለመጠበቅ ቁርጠኛ ነን።
- በቅርብ ጊዜያት ባለው የ Covid-19 ተጠቂዎች ቁጥር መጨመር ላይ ተመርኩዞ፣ King County ማህበረሰባችንን ለመጠበቅ የሚረዱ ደንብ አውጥቷል ይህም በህዝብ ዝግጅቶች እና ተቋማት ላይ ያሉ ሰዎች እንዲከተቡ ወይም ኔጌቲቭ የ Covid-19 ምርመራ ውጤታቸውን እንዲይዙ ማረጋገጫ የሚጠይቅ ነው።
- King County በክልሉ መንግስት ድጋፍ ሰራተኞችንና ደንበኞችን ለመጠበቅ የክትባት ማረጋገጫ መስፈርቱን እንደ መሳሪያ አስተዋውቋል።
- የእኛ የኃላፊነት ድርሻ የንግድ ድርጅቶች ክፍት ሆነው እንዲቀጥሉ በማድረግ ለማኅበረሰባችን ሁሉ አስተማማኝና ጤናማ የሆነ አካባቢ ማቅረብ ነው። የክትባት ማረጋገጫ ከሁሉም የተሻለው መሳሪያ ነው ይህንን ማድረግ ይኖርብናል።



# ምስለ ሁኔታዎች

የ King County የክትባት ማረጋገጫ መስፈርት ማለት 12 አመት እና ከዚያ በላይ የሆናቸው ግለሰቦች የ Covid-19 ክትባት ማስረጃ ወይም ኔጌቲቭ የምርመራ ውጤት ማስረጃ ማሳየት አለባቸው ማለት ነው። ይሁን እንጂ የንግድ ድርጅቶች አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ ሌላ አማራጭ ሊያቀርቡ ይችላሉ። አማራጮቹ የሚከተሉትን ሊያካትቱ ይችላሉ፡-

- ደንበኞችን ከቤት ውጪ ባሉ ቦታዎች ላይ ማስቀመጥ
- ደንበኞችን በአካባቢው ከሚገኙ ተመሳሳይ አማራጮች ጋር ማገናኘት
- የሚወሰድ ምግብ መስጠት
- ከቤት ውጭ የጂምናስቲክ ቦታ ማቅረብ
- ደንበኞችን ወደ ምህዳራዊ መገልገያዎች መጠቆም

ያስታውሱ፣ የንግድ ድርጅቶች የማንንም አካለ ስንኩልነት ይሁን የደንበኞችን የተገለጸውን ነጻነትና ትክክለኛነት መመርመርም ሆነ መጠራጠር የለባቸውም። በተጨማሪም የንግድ ድርጅቶች ደንበኞችን በዘራቸው፣ በቀለማቸው፣ በቅድመ አያቶቻቸው፣ በብሔር መነሻቸው፣ በትውልድ ቦታቸው፣ በፆታቸው፣ በእድሜ፣ በሃይማኖት፣ በእምነት፣ በአካል ጉዳት፣ በወሲብ ሁኔታ፣ በፆታ ማንነት፣ በክብደት ወይም ቁመት ላይ ተመስርተው በተለያየ መንገድ ማስተናገድ የለባቸውም።

የንግድ ድርጅቶች ይህን ለማድረግ ፈቃደኛ ካልሆነ ትዕቢተኛ ወይም ዓመፀኛ ከሆነ ደንበኛ ጋር በአካል ለመግጠም ፈጽሞ መሞከር የለባቸውም። ከዚህ በታች የንግድ ድርጅቶች ሊያደረጉዋቸው የሚችሉ ግንኙነቶችን ለመገመት የሚረዱ ሁኔታዎችን ያገኛሉ።

- ደንበኛ/ሸማች ካለባቸው የጤና ችግር ወይም የአካል ጉዳት ጋር ተያያዞ ክትባት ማግኘት እንደማይችሉ ይናገራሉ
    - የንግድ ድርጅቶች እንደ አማራጭ ኔጌቲቭ የ Covid-19 ምርመራ መጠየቅ ይችላሉ። ይህ ምርመራ በማንኛውም የዝግጅት ቦታዎች የሚቀርብ ወይም የ PCR ፈጣን ምርመራ ሊሆን ይችላል። የቤት ውስጥ ምርመራዎች ትክክል አይደሉም።
    - ደንበኛው/ሸማቹ ኔጌቲቭ የ Covid-19 የምርመራ ማስረጃ ከሌለው፣ ወይም ለማሳየት ፈቃደኛ ካልሆነ፣ የንግድ ድርጅቶች የውጭ አማራጮችን፣ የማድረስ ወይም፣ የሚቻል ከሆነ፣ ምግብን ይዞ የመሄድ አማራጮችን ማቅረብ ይችላሉ።

- ደንበኛው/ሸማቹ የክትባት ማረጋገጫ ወይም ኔጌቲቭ የ Covid-19 ምርመራ ውጤት ማሳየትን ከተቃወሙ
    - የንግድ ድርጅቶች ይህ የ King County ደንብ እንደሆነና ተቋሙ ያለ ማረጋገጫ የቤት ውስጥ አገልግሎት መስጠት እንደማይችል ማስረዳት ይችላሉ።
    - የንግድ ድርጅቶች እንደ ምግብን ይዞ የመሄድ አማራጮችን ወይም ማድረስንን የመሳሰሉ አማራጮችን ሊያቀርቡ ይችላሉ።
    - የንግድ ድርጅቶች ይህን ደንብ ለማስፈጸም የተቻላቸውን ሁሉ ማድረግ አለባቸው ነገር ግን ለደንበኞች ባህሪ ተጠያቂ አይሆኑም።

- ደንበኛው/ሸማቹ የሚያስፈራራ ወይንም አመጸኛ ከሆነ
    - ሸማቹን ከተቋሙ እንዲወጣ ይጠይቁ። አይጣሉት ወይም አይዛቱበት። ተጨማሪ ጠቃሚ ምክሮችን ለሚያስፈራራ ሰው ምላሽ ለመስጠት ከ Crisis Prevention Institute (የቀውስ መከላከያ ተቋም) ያግኙ።
    - ወደ 911 ይደውሉ እና በ 206-477-3977 ወደ King County ሪፖርት ያድርጉ። ድንገተኛ ምላሽ የሚሰጡ ሰዎች መጠራት ያለባቸው አንድ ደንበኛ ስጋት ላይ ከወደቀ ወይም ዓመፀኛ ከሆነ እንጂ የክትባት ማረጋገጫ ፖሊሲውን በተደጋጋሚ ለማስፈጸም አይደለም።

- አንድ ግለሰብ የቤት ውስጥ ፈጣን የ Covid ምርመራ ያመጣል
    - የቤት ውስጥ ምርመራዎች በዚህ ደንብ መሠረት ተቀባይነት የላቸውም። ምርመራዎቹ በምርመራ ቦታዎች ላይ የሚቀርቡ ወይም የ PCR ፈጣን ምርመራ በህክምና ባለሞያ የሚሰጡ መሆን አለባቸው።
    - እነዚህ ግለሰቦች የውጪ አማራጮች ሊቀርብላቸው ይችላል።

- ግለሰቡ የክትባት ማረጋገጫ የለውም ወይም ኔጌቲቭ የ Covid-19 ምርመራ ውጤት አያቀርብም፤ ነገር ግን ወደ ቤት ውስጥ ሲገቡ ማስክ ለማድረግ ቃል ይገባሉ
    - ማስክ ማድረግ ተጨማሪ አይደለም። የንግድ ድርጅቶች በውጭ ላሉ ወይም እንዲገለገሉ ለሚፈቅዱላቸው ደንበኞች ምክንያታዊ የሆኑ አማራጮችን ማቅረብ ይችላሉ።

- ግለሰቡ ምንም ነገር ለመብላትም ሆነ ለመጠጣት ስላላቀዱ የክትባት ማረጋገጫ መስጠት እንደማያስፈልገቸው ይናገራሉ
    - ይህ ደንብ ለሁሉም ግለሰቦች 12 አመት እና ከዚያ በላይ ለሆናቸው ዝግ በሆኑ ተቋማት እና በህዝባዊ ዝግጅቶች ላይ ይሠራል። ይህ ግለሰብ የክትባት ማረጋገጫ፣ ኔጌቲቭ የ Covid-19 ምርመራ ውጤት ማስረጃ ማቅረብ ወይም በውጭ አማራጮች መገልገል ያስፈልገዋል

- የንግድ ድርጅቱ ደንበኛው የሐሰት የክትባት ማስረጃ ወይም የ Covid-19 ምርመራ እያቀረበ ነው ብለው ይጠረጥራሉ።
    - ይህ በመተማመን ላይ የተመሠረተ ደንብ ነው። የንግድ ድርጅቶች አቅማቸው የፈቀደውን ያህል መደገፍና አለመግባባት ውስጥ መግባት የለባቸውም።

- ቀደም ባለ አጋጣሚ የክትባት ማስረጃቸውን ያሳዩ ደንበኛ በድጋሜ ለመገልገል ሲመጡ እንደገና ማረጋገጫ ማሳየት ያስፈልጋቸው እንደሆነ ይጠይቃሉ
    - ደንበኛው/ሸማቹ በእያንዳንዱ ጉብኝታቸው ላይ የክትባት ማረጋገጫ ወይም ኔጌቲቭ የ Covid-19 ምርመራ ውጤት ማቅረብ አለባቸው።



# ምልክት

*እንግሊዝኛ ምልክቶች ብቻ እዚህ ይገኛሉ*

- *8x11 ምልክት*
- *11x17 ምልክት*



# መገልገያዎችን ያግኙ

- ይፋዊ የ King County Health Order
- የ King County Public Health (የ King County የህብረተሰብ ጤና) ተደጋጋሚ ጥያቄዎች
- የ Seattle Metro Chamber (የሲያትል ሜትሮ ምክር ቤት) - የንግድ መርጃዎች
  - KCVaxVerified.com
- የእንግሊዘኛ ብቻ ንግድ ምልክት
  - 8x11 ምልክት
  - 11x17 ምልክት
- የሰራተኞች ስልጠና መምሪያ
- ውስን የእንግሊዝኛ ብቃት ላላቸው መርጃ መስመሮች፡-
  - አማርኛ፡- 206-825-4240
  - አረብኛ፡- 206-486-2669
  - ኮርያኛ፡- 425-776-2400
  - ሶማልኛ 253-317-3251
  - ስፓኒሽ፡- 888-502-9597
  - ትግርኛ፡- 206-486-2669
  - የመንደሪን እና ካንቶኒዝኛ መረጃ ማዕከል
    - ከ 55 አመት በላይ የሆኑ ሰዎች፡- 206-816-4991
    - ከ 55 አመት በታች የሆኑ ሰዎች፡_ 206-330-4627



## በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎች

ይጎብኙ:- kcvaxverified.com/faq